# መቅድሕ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፯ ቀን: የካቲት፩ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ




## ሁለት ተጻጻሪ የሽግግር አይነቶች!

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በቅርብ ለህዝብ የሽግግር ሰነድ ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው። የዚህን ሰነድ ውስጠ ፍልስፍና ምንነት በሚገባ መተንተንና ለህዝባችን ብቸኛው አማራጭ መሆኑን የማሳየት በድርጅቱ ላይ የወደቀ ሀላፊነት መሆኑን ይገነዘባል። በዚህ አኳያ ህዝባዊ የሽግግር ጊዜ ስንል የህዝባችንን ህይወት ከመቀየሩ አኳያ ስለሚጫወተው ሚና በዝርዝር ማሳየት አስፈላጊ ነው። እናም በተጓዳኝ ከዚህ የድርጅታችን የሽግግር ሰነድ በተጻራሪ የቆመውን የሽግግር አስተሳሰብን ምንነት ማሳየትም ተገቢ ነው። የሚስማማውን መርጦ የመውሰድ የህዝብ ይሆናል።

በቀጥታ የድርጅታችንን የሽግግር ሰነድ ምንነት ከማውሳታችን በፊት ባገራችን ከዚህ በፊት የነበሩ አጥፊ የሽግግር ታሪኮቻችንን ባጭሩ መዳሰስ አስፈላጊ ነው።

የመጀመሪያው ከእምዬ ምንሊክ ህልፈት በኋላ በተፈሪ መኮንንና በአልጋወራሹ በልጅ ኢያሱ ምንሊክ መሀል የተነሳው አስቸጋሪ የሽግግር ታሪክ ነው። የዚህ የሽግግር ጊዜ ዋና መገለጫዎች ተብለው ሊገለጡ የሚችሉት ሶስት ኩነቶች ናቸው።

አንደኛው ዘመናዊነትን በሚደግፉት በተፈሪ መኮንንና በወግ አጥባቂው በኢያሱ ምንሊክ መሀል የነበር በሀሳብ ተፍታቶ ያልተገለጠ ግጪት፣ ሁለተኛው በወቅቱ የተነሳው የአንደኛው የዓለም ጦርነት ላይ ሁለቱ ሰዎች የነበራቸው አቋም መለያየት ነበሩ። ሶስተኛው ከነዚህ የስልጣን ተፋላሚዎች በስተኋላ የቆሙት የውጭ ተጸኖ ፈጣሪ የሆኑ የወቅቱ አቅኚዎች አፍራሽ ሚና ነበር። እነዚህ አፍራሽ ሀይሎችም ከተፈሪ መኮንን ኋላ የተባበረው የእንግሊዝ መንግስት፣ ፈረንሳይና ተባባሪዎቻቸው የቆሙ ሲሆኑ ከአልጋ ወራሹ በስተኋላ የቆመው የዘመኑ የአካባቢው ሀይል ቱርክና የጦር ቃልኪዳን ተባባሪው ጀርመን ነበር።

# ሁለት ተጻጻሪ የሽግግር አይነቶች

ይህን የታሪካችንን ወቅት ልዩ የሚያደርገውም ለመጀመሪያ ጊዜ የውጪ ሀይል በሀገሪቱ አስተዳደር ውስጥ አንጃ የመፍጠርና እግረመንገዱንም ጥገኛ አሻንጉሊት የገዢ ሀይል የማስቀመጥ ታሪክ እዚህ ላይ መጀመሩ ነው። ባጭሩ የኢትዮጵያ ገዢዎች ስልጣናቸውን ከህዝብ ለመከላከል የሚያስችላቸውን እርዳታ በማግኘት ለውጥ ለሀያላን ጥቅም መጠበቅ የማጎብደድ ታሪክ የተቋጠረው በዚህ የሽግግር የታሪክ መራፍ ላይ እንደነበር አስረግጦ መያዝ ይገባል።

በዚያ የሽግግር ትግል ተፈሪ መኮንን አሸናፊ ሁነው ለመውጣት ከረዷቸው ከመራባውያን መንግስታት ጋር የፈጠሩት የግኙኝነት አይነት ታሪክ ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ መጋብት አስፈላጊ አይደለም።

ሁለተኛው የሽግግር ታሪክ አስቸጋሪና በዘመናዊው ታሪካችን ደም አፋሳሽ የሆነው የሽግግር ጊዜ ከ66 አብዮት ቀጥሎ የመጣው የደርግ አገዛዝ ነው። ሽግግሩን ለመምራት በተፎካካሪነት የቀረቡት ሁሉም ከአንድ የህብረተሰብ ክፍል የመጡ ተደራጅን ያሉ ሀይሎች ነበሩ። ደርግን ጨምሮ። ሁሉም የህዝብ ውክልናን የሚያስገኝ የፖለቲካ ፕሮግራም አለን ባዮች ነበሩ። ይሁንና ህዝባዊ የሚመስል ሽጋ ፕሮግራም በራሱ የሚፈይደው ነገር እንደሌለ የተረዳንበት ወቅት አልነበረም።

ሁሉም በመርህ ደረጃ ሊጨብጡት የተቸገሩት ውክልና የሚገለጠው ህዝቡ ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሁኖ ያለምንም መገፋት በራሱ ውሳኔ በነጻነት በሚሰጠው ድምጽ ብቻ የሚገለጥ መሆኑን ነው።

ስለሆነም በአብዮቱ ወቅት ሁለት የሽግግር አይነት ያቀረቡ ወገኖች መሀል ህዝቡ ያልተወከለና ባይተዋር እንደነበር የሚታወስ ነው። እናም በመሀከላቸው በተከተለ አመጽ አሸናፊው ደርግ የሽግግሩን ዘመን ጠቅልሎ ያዘ። ለአገዛዝ መደላድሉ የሚያስፈልገውን የውጭ እርዳታም ከሶሻሊስት ሀገሮች አገኘ። ምን እነደተከተለ ሁሉም ያለፈበት ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ አንገባም።

ሶስተኛው የሽግግር ጊዜ ሲጀመር ሀገርን እንደሀገር በመክዳት ተደራጅቶ በመጣው የትግሬ ወያኔ ተጀመረ። እናም ኢትዮጵያን እንደሀገር ለማፍረስ የመጣው የትግሬ ወያኔ የጥፋት ሀይልና ተባባሪዎቹ ላለፉት 27 ዓመታት ሀገሪቱን በማፍረስ፣ የህዝቧን አንድነት በመበትንና በዐማራው ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል በመፈጸም በሂደት ላይ ያለና ዛሬም ያላባራ የእልቂት አዝመራውን እየሰበሰበ ነው። ይህ ወንጀለኛ የጥፋት ሀይል ዛሬም ህዝባችን ላይ የሚያወርደው መአት ምስክር ነው።

የትግሬ ወያኔ መውደቁ ነው። መቼ? ቅጽበታዊ በሆነ ሁኔታ ባልጠበቅንበት ወቅት ውስጥ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

# ሁለት ተጻጻሪ የሽግግር አይነቶች

ለዚህ ሁኔታ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ወሳኝ ጉዳይ ሁኗል። የዐማራ ህልውና የኢትዮጵያ አንድነት ድርጇት የሽግግር ሰነድ የተዘጋጀው ከዚህ ሀገራችን ከገባችበት አጣብቂኝ ትወጣ ዘንድ ከላይ የተገለጡ የተሰናከሉ የፈላጭ ቆራጭ የዘውድ አገዛዝን፣ የደርግ አምባገነንነትንና በዘር ማጥፋትና በዘረፋ ላይ የተመሰረተን የትግሬ ወያኔን የወለደ የሽግግር ስርአትን በሚገባ ካጠና በኋላ ህዝቡን ማእከል ያደረገ የሽግግርን አስፈላጊነትን በመገንዘብ ላይ የተመሰረተ ነው።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የሽግግር ሰነዱን ሲያዘጋጅ ከላይ ያለፍናቸውና ዛሬም ገና በደም እየከፈልንበት ያለ የፖለቲካ ስህተትን ላለመድገም በሚል ዋና ሀሰብ ላይ ያጠነጠነ ነው። ዛሬ ሀገራችን ከገጠማት አደገኛ መስቀለኛ መንገድ ላይ የሚያዋጣትን ጎዳና ያለምንም መሳሳት ትመርጥ ዘንድ ይበጃታል ያልነው አቅርበናል።

ግለሰቦች፣ ግለሰቦችም በቅንነት ተሰባስበው ድርጇት በመፍጠር ታግለው የህዝባቸውን ምኞት እውን ለማድረግ መነሳታቸው በራሱ የሚደገፍ ነው። ይሁንና ቅንነትና ምኞት ብቻውን ለህዝባዊ ስልጣን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት አይሁንም። ህዝብ ፊት ቀርቦ የህዝብን ይሁንታ ማግኘት የግድ ልንከተለው የሚገባ በምንም የማይለወጥ መመሪያ ሊሆን ይገባል። የዐማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጇት መመርያ ከዚህ መርህ ይመነጫል። ዛሬ በአንዳንድ በተቧደኑ ወገኖች በኩል የዱሮውን የተሳሳተ ጎዳናን ለሀገራችን እንደመፍትሄ አድርጎ የቀረበ የሽግግር ሰነድ ተመራጭ ነው ብለን አናምንም። ሀገራችን ዳግም በዚያ የጥፋት ጎዳና ካመራች ከናካቴው ያልቅላታል የሚል እምነታችን የጸና ነው። ከመረጥነው የጥፋት ጎዳና እንውጣ። ከህዝባችን ምኞት ጋር የማይሄድ ተጻራሪና የባለህበት እርገጥ አመለካከት ነው ይታረም እንላለን። ተራማጅ ሀሳብ አይደለም ብለን እንሞግታለን። ይህንን በድርጇታችን የቀረበውን በህዝብ ውሳኔ የማደርን መመሪያ በመቀበል ለሀገራችን የምናተርፋቸው መሰረታዊ የሆኑ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው።

የሽግግር ጊዜው በህዝብ በተመረጠ ሸንጎ ቢመራ ከዚህ ህዝባዊ ሸንጎ በርግጠኝነት ሀገራችንን የሚመራ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ይወለዳል።

የሽግግር ጊዜው በህዝብ በተመረጠ ሸንጎ ቢመራ የሉዓላዊ ሀገር አንድነት የተረጋገጠ ይሆናል።

የሽግግር ጊዜው በህዝብ በተመረጠ ሸንጎ ቢመራ የህዝቧ አንድነት፣ ሰላምና እድገት በጠነከረ መሰረት ላይ እንዲዋቀር ፈሩን ይቀዳል።

የሽግግር ጊዜው በህዝብ በተመረጠ ሸንጎ ቢመራ ካለፉት ታሪካችን ጋር ተቆራኝቶን ከመጣና ዛሬም ካለቀቀን ለውጭ መነግስታት አሻንጉሊት የመሆን ታሪክ ጋር እንለያያለን።

የሽግግር ጊዜው በህዝብ በተመረጠ ሸንጎ ቢመራ ህዝባችን ሳይለቀው ከመጣ በነገድ ጥላቻና አላስፈላጊ የሆነ ፉክክር፣ የዘር ማጥፋት እልቂትና ጦርነት፣ ከጦርነት ከሚወለዱ ኋላ ቀርነትና ሰላም የማጣት አባዜ ተላቆ ለእድገት የሚበቃበት ዘመን ይከፈትለታል።

# ሁለት ተጻጻሪ የሽግግር አይነቶች

የዐማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ያለፉት ታሪኮቻችንን ባክብሮት ያስባቸዋል። ከታሪካችን ውስጥ ለጥፋት የዳረጉንን ለይቶ የማውጣትና ትምህርታዊ እንዲሆኑ ማድረግ የትውልድ ሀላፊነት ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ባለፉት የቅርብ ጊዜ ታሪኮቻችን የነበሩትን ችግሮቻችንን ስንመረምር መንስኤዎቻቸውን ለይቶ ማወቅ ተገቢ ይሆናል። ከዚህ አኳያ የትግሬ ወያኔን የጥፋት የሽግግር ጊዜን እንደ ታሪካችን አካል አድርገን አንመለከትም። ይህ የጥፋት መልክተኛ በታሪካችን አስቸጋሪ ወቅት ላይ በውጭ ሀይሎች ተኮትኩቶ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የመጣ የጥፋት ሀይል ነው። እናም ባታሪካችን ውስጥ እውቅናን ሊያገኝ የማይገባው የጥፋት ክስተት ነው ብለን እናምናለን።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጂት የሽግግሩን ሰነድ ሲያዘጋጅ የተለያዩ ድርጂቶች እንደቀድሞው ህዝብን ያገለለና የውጭ ሀይሎችን ይሁንታን ማእከል ያደረገ የሽግግር ሰነድ እንደአዘጋጁ ያውቃል። ይህንንም ሰነዳቸውን ለህዝባችን ይፋ አድርገዋል። ሁለት ተጻጻሪ የሽግግር አይነቶች ለህዝቡ ቀርበዋል። ህዝቡ የሚበጀውን ይመርጣል። ይሁንና በኛ እምነት ይህ ምርጫችሁ የመጣንበት የጥፋት ጉዳና ነው አንድገመው ለህዝባችንም አይበጅም እንላቸዋለን። ከህዝባችንም የወቅቱ የትግል ጥሪ ጋርም ስምም አይደለም እናም መንገዳችሁን ቀይሩና የህዝቡን ጎዳና ተቀላቀሉ እንላለን። እንደትናንቱ ሁሉ ህዝባችንን አግልሎ፣ በውጭ ሀይል ተኮድኩዶ ከሚያዝ የሽግግር ስልጣን ውስጥ የሚወለደው አምባገነን ስርአት ነው እንላቸዋለን። ህዝቡ የራሱን እንደራሴዎችን መርጦ ሽግግሩን ይምራ። የሚመስለውንና ለሱ የሚስማማውን የውስጥ የአስተዳደር አይነት ይምረጥ። ከኛ የሚጠበቅ በሱ ውሳኔ መገዛት ብቻ ነው። የኛ ተግባር ስልጣን የህዝብ መሆኑን ማወቅ ነው። በስልጣኑ እሱን መተካት የሱን ስልጣን መንጠቅ ይሆናል። ሀገሩንም ለባዳ አስላፎ የመስጠት አባዜ ይከተላል። የሱ ስልጣን አገልጋዮች ሁነን መስራት የኛ ብቸኛው ተግባር መሆኑን እንገንዘብ። አገልጋዮቹ ነን። በትግሬ ወያኔን ህገመንግስት ተብዬ የተቋቋመውን ስርአት እንዲጸና ምኞት ያላቸውን በቋንቋ ላይ የተመሰረቱ ድርጂቶችንም ከኋላ ቀር አመለካከታችሁ ጽዱ፣ ከህዝቡ የአንድነት መንፈስ ጋር ለመራመድ ተነሱ እንላለን። መገንጠል የህዝቡ ፍላጎት አለመሁኑን በትግሉ እያሳያችሁ ነው እንላለን።

በዚህ እውቅና ላይ መግባባት ካለ በዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጂት አማካኝነት የወጣው የሽግግር ሰነድ የሁሉም ሰነድ ይሆናል የሚል እምነታችን የጸና ነው። በዛሬው የፖለቲካ አየር ላይ ያለውና ደጋግመን እንዳሳየነው ብቸኛው ህዝቡን ማእከል ያደረገ የሽግግር ሰነድ የኛው ሰነድ ብቻ ነው። ሰነዱንም ህዝባችን እንዲረዳው ለማድረግ በሚደረግ ዘመቻ ሁሉም ለህገሩ ደግ አሳቢ ዜጋ የሆነ ሁሉ አብሮን እንዲቆም ጥሪ እናቀርባለን። ግዴታውም ነው የሚል የጸና እምነት አለን።

ውድ እናት ሀገር ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር!!